# <u>በዴንማርክ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም</u>
# <u>በደመቀ ሆኔታ ለማክበር ዝግጅቱ ተጠናቋል</u>

በመላው ዴንማርክ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ጳጉሜ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. (September 11, 2007) የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ኣሸብራቂ በሆነ ሆኔታ ለማክበር ዝግጅታቸውን ኣጠናቅቀዋል፡፡

የዴንማርክ ርእሰ ከተማ የሆነችው የኮፐንሃገን ከተማ ማዘጋጃ ምክር ቤት የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በደመቀ ሆኔታ ሲከበር የከተማዋ ነዋሪዎችና ኣገር ጎብኚዎቿ በቀላሉ የበዓሉ ተካፋዮች እንዲሆኑ ለማስቻል በከተማዋ እምብርት የሚገኝና "ኣማየርቶርቭ" በመባል የሚታወቀውን ሰፊና ዝነኛ ኣደባባይ የበዓሉ መከበሪያ ስፍራ እንዲሆን ፈቅዷል።

የሚሌኒየሙ ክብረ በዓል የሚከበርበት ልዩ ስፍራ ኣቀማመጥ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የከተማዋ ነዋሪዎችና ኣገር ጎብኝዎች የመማረክ ባህርይ ያለው እንደመሆኑ መጠን፣ በዓሉን በስነስርዓትና በምቾት ለማክበር ይቻል ዘንድ የከተማዋ ባለስልጣኖች ኣስፈላጊውን የጥበቃና የፀጥታ ኣስከባሪ ሃይል በበቂ መጠን እንደሚሰማራ ለበዓሉ ኣዘጋጅ ኮሚቴ በሰጡት መግለጫ ኣረጋግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሚሌኒየም የኣፍሪካ ሚሌኒየም ጭምር ሆኖ እንዲከበር በስምንተኛው የኣፍሪካ ህብረት መደበኛ ጉባኤ የተሳተፉት የኣፍሪካ መሪዎች መወሰናቸው ይታወቃል፡፡ የወቅቱ የኣፍሪካ ህብረት ሊቀ-መንበር የጋና ፐሬዝዳንት እንደመሆናቸው መጠን፣ ይህንን የኣፍሪካና የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ታላቅ ክብረ በዓል በዚች ውብ የስካንዲናቪያ ከተማ በሚከበርበት ወቅት የበዓሉ የክብር እንግዳ ሆነው የተጋበዙት በዴንማርክ የጋና ሬፐብሊክ ኣምባሳደር የሆኑት ክብርት ኣምባሳደር ማውሪን ኣሜማቴክፖር (**Ambassador Maureen Amematekpor**) ናቸው። በክብርት ኣምባሳደሯ ኣማካኝነትም በዴንማርክ የሚኖሩ የሌሎች የኣፍሪካ ኣገሮች ኣምባሳደሮችና ባጠቃላይ በዴንማርክ የሚገኙ የዲፐሎማቲክ ማህበረ-ሰብ ኣባላት እንዲጋብዙለት የበዓሉ ኣዘጋጅ ኮሚቴ ኣምባሳደሯን በደብዳቤ ጠይቋል፡፡

በሚለኔየሙ ክብረ በዓል ከሚቀርቡት በርካታ ዝግጅቶች መካከል፤ በባህላዊ መንገድ የተዘጋጀ ቡና ለተጋባዦች ማስተናገድ፣ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄር/ብሄረ-ሰቦች ባህሎች የሚያንፀባርቁ ትርኢቶች ማቅረብ፣ የኢትዮጵያ ኣዲስ ገፅታ የሚያንፀባርቁ ፊልሞች በትልቅ ስክሪን ማሳየት ይገኙበታል፡፡

የበዓሉ ወቅታዊ መፈክር <u>"በኢትዮጵያ ምድር ድህነትን ያለፈ ታሪክ ብቻ ሆኖ እንዲቀር እናደርጋለን</u>" የሚል ነው፡፡

ከዚሁ ታላቅ ክብረ-በዓል ጋር በተያያዘ ቅዳሜ መስከረም 4 ቀን 2000 ዓ.ም. በዴንማርክ ለሚኖሩ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ክፍት የሆነና፣ የተጋበዙ ኣፍሪካዊያን፣ የዴንማርክና የሌሎች ኣገሮች ዜጎች የሚሳተፉበት ሌሊቱን በሙሉ የሚዘልቅ የኢትዮጵያ የባህል ምግቦች፣ መጠጦችና ዘፈኖች የሚያካትት ታላቅ መስተንግዶ በሰፊ ኣዳራሽ ተዘጋጅቷል፡፡

በሁለቱም ቀናቶች በሚቀርቡ ዝግጅቶች ጣልቃ የተለያዩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች የኢትዮጵያን ታሪክ በማስመልከት፣ ኢትዮጵያ ለኢንቬስተሮች ያላት እምቅ ሃብትና ኣመቺ የኣየር ንብረት፣ ለኣገር ጎብኚዎች ያላት ልዩ ብቃትና ፀጋ፣ የህዝቧ ሰው ወዳድነትና እንግዳ ተንከባካቢነት የመሳሰሉትን በማስረዳት የተለያዩ ቅስቀሳዎችና ገለፃዎች ያደርጋሉ፡፡

በዴንማርክ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ምንም እንኳ ምኞታቸው የሚሌኒየሙ ታላቅ ክብረ በዓል በሚወዷትና በሚኮሩባት ኣገራቸው በህዝባቸው መሃል ተገኝተው ማክበር ቢሆንም፣ በተለያዩ የስራና የልጆች የትምህርት-ቤት ጉዳዮች ያለመመቸት ምክንያት ይህንኑ ጥልቅ ምኞታቸው ለማሳካት ኣልቻሉም፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ታላቅ ኣጋጣሚ ተጠቅመው ለኣገራቸውና ለህዝባቸው በሚጠቅም ሆኔታ ለማክበር በውጭ መገኘታቸው በጎ ገፅታ ያለው መሆኑንም በሚገባ ይገነዘባሉ፡፡

በዴንማርክ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ኣዲሱ ሚሌኒየም የሰላም፣ የጤና፣ የደስታና የእድገት ኢንዲሆንላቸው ከልብ እየተመኙ፣ ህዝቦቻችንና መንግስታችን ድህነትን ከኢትዮጵያ ምድር ለማስወገድ እያደረጉት ያለውን ርብርብ ለማሳካት እያንዳንዳቸው በዴንማርክ የኢትዮጵያ የልማት ኣምባሳደሮች በመሆን የበኩላቸውን የዜግነት ኣስተዋፅኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናቸውን በዚህ ኣጋጣሚ ቃል ይገባሉ፡፡

## መልካም ሚሌንየም ለኢትዮጵያ ህዝቦች!
## ድህነትን ታሪክ ሆኖ እንዲቀር እናደርጋለን
## በዴንማርክ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል ኣዘጋጅ ኮሚቴ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com